# የእውነታ ሉህ ቁ. ፮

# የዘር ልዩነት ድህነት በገቢ እና ማኅበራዊ ድጎማ ላይ ያለው ተጽዕኖ


## የዘር መለየት ድህነት በገቢ እና በማኅበራዊ ድጎማ በኩል ምንም ስሜት ያመጣል?

**የጾታ ክፍያ ልዩነት፦** በቅርብ ጊዜ የመጡ ስደተኞች (እ.ኤ.አ. ከ2015-2016 የደረሱ) ስደተኞች ካልሆኑት ጋር ሲነፃፀር የ37% የገቢ ልዩነት ያጋጥማቸዋል ::
 በቅርብ ጊዜ የመጡ ስደተኛ ሴቶች ገቢ ስደተኛ ካልሆኑት ወንዶች ጋር ሲነፃፀር የ 59 በመቶ የገቢ ክፍያ ልዩነት ያጋጥማቸዋል፡፡ በቅርብ ጊዜ የመጡ በዘር የተለዩ ስደተኛ ሴቶች የገቢ ክፍያ ክፍተቱም ከፍተኛው ሊሆን ይችላል፡፡
**የቀለም ኮድ፦** በኦንታሪዮ ውስጥ እ.ኤ.አ. በ2015 አንድ ነጭ ወንድ ከሚያገኘው ከእያንዳንዱ ዶላር መጠን ሲነጻጸር በዘር የተለዩ ሴቶች 58 ሳንቲሞች ሲያገኙ በዘር የተለዩ ወንዶች ደግሞ 76 ሳንቲም አግኝተዋል፡፡ የ‘ቀለም-ኮዱ’ እስከ ሁለተኛ ትውልድ ባለቀለም ሠራተኞችም ይቀጥላል፡፡
**የልዩነት ተጽዕኖ፦** በዘር የተለዩ ነዋሪዎች በዝቅተኛ ገቢ ስታቲስቲክስ በብዛት ይሠራሉ፡፡፡
በ2016 ላይ የቀለም ሰዎች  ያገኙት ዝቅተኛ ገቢ መጠን 21.3% ሲሆን በዘር ያልተለዩ የኦንታሪዮ ኗሪዎች ደግሞ 11.5% ነበር፣ ይህም ዝቅተኛ ነው፡፡
12% ከሚሆኑት በዘር ካልተለዩ ነዋሪዎች ጋር ሲነጻጸር  በዝቅተኛ ገቢ የሚኖሩ በዘር የተለዩ ካናዳውያን ነዋሪዎች 21% ይሆናል፡፡
**ኢሚግሬሽን፦** በቅርብ ጊዜ የመጡ ስደተኞች ዝቅተኛ ገቢያቸው 31.4% ሲሆን ስደተኞች ያልሆኑ ከሚያገኙት 12.5% ጋር ሲነጻጸር መጠኑ እጥፍ ጊዜ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በዘር የተለዩ ስደተኞች ዝቅተኛ የገቢ ክፍያ የማግኘት ዕድላቸው በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡
**የሕዝብ ጤና፦** በማኅበራዊ ድጎማ ድጋፍ ሥር ያሉ አያሌ ሰዎች ድሃ ካልሆኑት ይልቅ በሕይወታቸው አልፎ አልፎ ራስን የማጥፋት እርምጃ ያስባሉ፤ እስከ 20 ጊዜ ያህል ራሳቸውን የመግደል ሙከራ ያደርጋሉ፡፡
ነባር የአገሬው ተወላጆች እና ባለቀለም ሰዎች አነስተኛ የህክምና እና የአእምሮ ጤና ድጎማ ያገኛሉ፡፡ በዚህም ብዙ ጊዜ ላልተመጣጠነ ተዛማጅ ጉዳትና አደጋ ይዳረጋሉ፡፡

**በአደገኛ ሥራ መሠማራት፦** የዘር ልዩነት ያላቸው ሰዎች - ነባር የአገሬው ተወላጆች፣ ባለቀለም ሰዎች - እና ስደተኞች አደገኛ በሆኑና ዝቅተኛ ደሞዝ በሚከፈልበት፣ ጥቅማ ጥቅም-የለሽ፣ ዋስትና-የለሽ ሥራ ላይ በብዛት ተሠማርተዋል፡፡
**የገቢ ክፍያ ልዩነት፡** እ.ኤ.አ. በ 2016 በዘር በተለዩና ባልተለዩ ሰዎች የነበረው የገቢ ክፍያ ልዩነት ከ25% ወደ 26% ብሔራዊ እድገት አሳይቷል፡፡


## ነባር የአገሬው ተወላጅ ትኩረት

በቶሮንቶ ውስጥ በ2018 የተደረገው የጤና ጥናት ሪፖርት እንደሚያሳየው 87% ነባር የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ውስጥ ከአንድ ቤተሰብ ገቢ ቀረጥ ከመቆረጡ በፊት 70% ወይም ከዚያ በላይ የሚሆን ለምግብ፣ ለመጠለያና ለልብስ ላይ የሚያጠፉ እና በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ ናቸው፡፡




ነባር የአገሬው ተወላጅ ሕጻናት ኢንዲጅኖስ ካልሆኑት ይልቅ ሁለት ጊዜ ዕጥፍ ለድህነት ይጋለጣሉ፡፡
ስለሆነም በነባር የአገሬው ተወላጅ እና ተወላጅ ባልሆኑት ህዝቦች መካከል ቀጣይነት ያለው ትልቅ የገቢ ልዩነት አለ፡፡
በ2016 የተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መረጃ በአገሬው ተወላጅ ሴቶችና የአገሬው ተወላጅ ባልሆኑ ወንዶች መካከል የ45% የገቢ ክፍተት የታየ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የአገሬው ተወላጅ እና ተወላጅ ባልሆኑት በሁሉም ክፍሎች መካከል ያለው የገቢ ልዩነት 33% መሆኑን ታውቋል፡፡
እ.ኤ.አ. በ2012 –13 ባለው ጊዜ ውስጥ ማኅበራዊ ድጎማ ከተቀበለው 5 በመቶ የካናዳ ሕዝብ መካከል 33.6 ከመቶ የሚሆኑት ቀደምት ህዝቦች (First Nations) ናቸው፡፡
በአንዳንድ የአገሬው ተወላጅ ማህበረሰቦች በማህበራዊ ድጎማ ከሚያገኙት 80% በላይ የሚሆኑት ናቸው፡፡ የነባር የአገሬው ተወላጆች የገቢ መጠንም በቀጥታ ከደረሱበት የትምህርት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ስደተኛ ሠራተኞች ምንም እንኳ ካናዳ ውስጥ እየሠሩ ለልዩ ልዩ ፕሮግራሞችም አስተዋጽኦ እያደረጉ ቢሆንም ማግኘት የሚገባቸውን የማኅበራዊ ጥቅማ ጥቅም መብቶች ሲነፈጋቸው ይታያል፡፡



**በካናዳ ውስጥ በድህነት የሚኖሩ ሁሉም ባለቀለም ሕዝቦች - ከተመረጡ የብሔረ-ነገድ ቡድኖች ጠቅላላ ድምር በመቶኛ (የካናዳ የሕዝብ ቆጠራ 2016)**




## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው። እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው።

ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው።

በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑቱ በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች የመጡ ናቸው። በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው።

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው። ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው።

**ስልታዊ ዘረኝነት** ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው።

የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል።

ስለኦንታርዮ ዳራ/ሠንጠረዥ የእውነታ ሉሆች የርዕስ ገጽን ይመልከቱ። የአገሬው ተወላጅ ሕዝብ ቆጠራ፦ የዝቅተኛ ገቢ መረጃ ያን ያክል ሪፖርት የለም። ለዚህም ምክንያቱ ብዙ የአገሬው ተወላጆች ከበፊቱና ከአሁኑ የቅኝ ግዛት ፖሊሲ የተነሣ በመንግስት ላይ ምንም ዓይነት እምነት ስለሌላቸውና ብዙ ስለ ማይሳተፉ ነው።

**ዝቅተኛ ገቢ፦** በኦንታሪዮ ውስጥ በተለያዩ የነገዶች-ዘር ያለ ዝቅተኛ ገቢ በመቶኛ ሲሰላ እንደሚከተለው ይሆናል፦አረቦች (40.6%)፤ ምዕራብ ኤስያውያን (36.1%)፤ ኮርያውያን (31.4%)፤ ጥቁሮች (24.1%)፤ ቻይናውያን (22.2%)፤ ላቲን-አሜሪካውያን (19.9%)፤ የደቡብ ምስራቅ ኤስያውያን (18.4%)፤ እንዲሁም ደቡብ ኤስያውያን (18.0%) - በተቃራኒው ባለ ቀለም ያልሆኑ ህዝቦች ገቢ 11.5% ነው።

# ምን እየተደረገ ነው?

ኢንካም ሰክዩሪቲ አድቮኬሲ ሰንተር [ISAC] ማለት በኦንታርዮ ማህበረሰብ ያለ የሕግ ክሊኒክ ሲሆን ተልዕኮው በኦንታሪዮ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የገቢ ዋስትናቸውን ማሻሻል፣ ማሕበረሰቡንም ማደራጀት፣ የልማት ፖሊሲንና የጥብቅና ሥራውንም መጠበቅ፤ እንዲሁም የክስ፣ ሙግትና ክርክር ሙከራ ስልቶችን ማሳደግ ነው። iincomesecurity.org / isac@lao.on.ca

እህትማነት - በፀረ-ዘረኝነት እና በፀረ-ጭቆና መርሆዎች የሚመራና በማህበረሰብ ላይ የተመሠረተ ነው። ተልዕኮውም ዝቅተኛ ገቢ ለሚከፈላቸው፣ የሚረባ ቤት ለሌላቸው ወይም ከነጭራሱ ቤት-አልባ የሆኑ ሴቶች አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ለመጠበቅ፣ ኢ-ፍትሃዊነትንና ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመለወጥና በአጠቃላይ የሴቶች ደህንነትን ለመጠበቅ ይሠራል። sistering.org / general_info@sistering.org